DOI http://dx.doi.org/10.4314/mlr.v8i2.9

# Title:

## **The Convention on the Recognition and Enforcement of Foreign Arbitral Awards:** Advantages, Disadvantages and Some Remarks on Ethiopia's Course of Action Ahead

Fekadu Petros Gebremeskel

## Summary

The Convention on the Recognition and Enforcement of Foreign Arbitral Awards, often referred to as the New York Convention, has established itself as a regulatory and enforcement instrument which is crucial to international trade. This is evident from the fact that more than 150 countries have so far ratified the convention. Although Ethiopia is one of the earliest signatories, it has not yet ratified the convention. Hence an inquiry into the possible rationale for Ethiopia's reluctance is necessary. Such an inquiry can only be made by comparing the advantages and disadvantages of ratifying the convention, as any decision to withhold ratification, after signing, must have been motivated by an assessment of the pros and cons of the Convention.

The advantages of ratifying the Convention are many. The major benefits include boosting a country's goodwill as business friendly and contract enforcing, helping a country borrow on lower rate of interest and enhancing investor motivation toward lower rate of return on investment, ease of enforcing contracts abroad for domestic parties, ease of attracting foreign investment, and so on. The disadvantages are mainly two: that of impairment on sovereignty like any other treaty, and elimination of the opportunity for domestic traders to avoid payment of international debts.

In view of the pros and cons higlighted above, it is fairly safe to conclude that there are more advantages than disadvantages in ratifying the 1958 New York Convention. This can be substantiated by the lack of any member country that has withdrawn from or renounced the Convention. Compared to the ICSID Convention from which some countries have withdrawn upon finding that its demerits outweigh its advantages, the absence of such withdrawals from the New York Convention indicates that ratifying it is not as worrisome as it is often thought from the outside. Therefore, it is high time for Ethiopia to consider ratifying this Convention.

# በውጭ አገር የተሰጡ የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች እውቅናና አፈጻጸም ስምምነት፡

## ጥቅሞች፣ ጉዳቶች እና ስለኢትዮጵያ ቀጣይ እርምጃ አንዳንድ ነጥቦች

*ፈቃዱ ጴጥሮስ ገ/መስቀል*[♣]

## *መግቢያ*

*የንግዱ ማኅበረሰብ በየዕለቱ ከሚገባባቸው ውሎች አፈፃፀም ጋር በተያያዘ በየጊዜው አለመግባባት ውስጥ ይገባል፡፡ እነዚህን አለመግባባቶች ለመፍታት በአብዛኛው ፍርድ ቤቶችን መጠቀም የተለመደ ቢሆንም ዘመናዊው የንግድ ሁኔታ ከሚጠይቀው ቅልጥፍና፣ ወጪ ቆጣቢነት እንዲሁም አስተማማኝነት አንፃር፣ ከፍርድ ቤት ይልቅ ግልግል ዳኝነት ተመራጭ እየሆነ መጥቷል፡፡ ምክንያቱም የግልግል ዳኝነት አንድን ጉዳይ ከጥቃቅን የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች ነፃ በሆነ ቀልጣፋ ሂደት በተከራካሪዎቹ ተመርጠው በሚሾሙና በጉዳዩ ላይ ልዩ ዕውቀትና ልምድ ባላቸው ዳኞች ውሳኔ እንዲሰጥ የሚያስችል የዳኝነት ዓይነት በመሆኑ ነው፡፡*

*ከዚህ አንፃር የግልግል ዳኝነት በዓለም ዓቀፍ ንግድ ውስጥ ተመራጭነቱ ከፍተኛ ነው፡፡ ከላይ በጠቀስናቸው ምክንያቶች የአገር ውስጡ ነጋዴ እንኳ ከአገሩ ፍርድ ቤቶች ይልቅ የግልግል ዳኝነትን ከመረጠ የሌላ አገር ዜጋ ከአገር ሰውም እጅግ በበለጠ የግልግል ዳኝነትን ይመርጣል፡፡ የውጭ ዜጋ በማያውቀው ሕግ፣ በማያውቀው የዳኝነት ሥነሥርዓት፣ ባህልና ቋንቋቸውን በማያውቃቸው ዳኞች ከመዳኘት ይልቅ የግልግል ዳኝነትን እጅግ አጥብቆ ይመርጣል፡፡ ይልቁንም፣ የግልግል ዳኝነትን ጉዳይ ከዐበይት የውል መደራደሪያ ነጥቦች መካከል አንዱ እንዲሆን በማድረግ በተዋዋዮች መካከል የሚፈጠር ማንኛውም አለመግባባት በግልግል ዳኝነት እንዲፈታ የሚያስችል አንቀጽ በውሉ ውስጥ ካልሰፈረ ውሉን አብዛኛውን ጊዜ አይፈርምም፡፡ ምክንያቱም የግልግል ዳኞች መምረጥን ጨምሮ፣ ሕግን የመምረጥ፣ ሥነ ሥርዓቱን፣ እንዲሁም የዳኝነቱን ቋንቋና ሥፍራ ወዘተ የመወሰን መብት ለተዋዋዮች ይሰጣል፡፡*

*የግልግል ዳኝነት በዓለም ዓቀፍ የንግድ ግንኙነት ውስጥ ትልቅ ቦታን ይይዛል፡፡ በዚህም ምክንያት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እ.ኤ.አ.* በ1958 *በኒው ዮርክ ከተማ ለፊርማ ያቀረበውን በተለምዶው የኒው ዮርክ ስምምነት* (New York Convention) *የተባለ ሰነድ በአሁኑ ወቅት* ከ150 *አገሮች በላይ አፅድቀውታል፡፡ ይህ ስምምነት በውጭ አገር የተሰጡ የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎችን እውቅናና አፈጻጸም የሚመለከት ሲሆን፣ በሰፊው እየተሠራበት ይገኛል፡፡ ምንም እንኳን ኢትዮጵያ የዚህ ስምምነት ተፈራራሚ ብትሆንም ስላላፀደቀችው በኢትጵያ ውስጥ ስምምነቱ አይሠራም፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ ጎረቤቶች እነ ጂቡቲ፣ ኬኒያ፣ ታንዛኒያ፣ ኡጋንዳ፣ ቡሩንዲ፣ ግብጽ እና ሌሎችም አያሌ የአፍሪካ መንግሥታት ስምምነቱን አፅድቀው*

[♣] በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ቤት ረዳት ፕሮፌሰር፣ ጠበቃና የሕግ አማካሪ፤ ኤል. ኤል. ቢ. እና ኤል. ኤል. ኤም. ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ኤል. ኤል. ኤም. ከሲዊዘርላንድ የጀኔቫ ዩኒቨርሲቲ በዓለም ዓቀፍ የግጭት አፈታት፡፡

እየሠሩበት ይገኛሉ፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ኢትዮጵያ በጣም እንደዘገየች መገንዘብ ይቻላል፡፡

ስምምነቱ ዓለም ዓቀፍ የግልግል ዳኝነትን በማቀላጠፍና ሥርዓት በማስያዝ ፈራሚ አገራት ተመራጭ የንግድና ኢንቨስትመንት መዳረሻ እንዲሆኑ የረዳ ከመሆኑም በላይ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የውል አፈፃፀምን ቀላልና አስተማማኝ አድርጓል፡፡ የማንም አገር ዜጋ በሌላ አገር ጥሪቱን አፍስሶ ሲሠራ፣ ወይም ደግሞ በሌላ አገር ካለ ሰው ጋር የንግድ ግንኙነት ሲመሰርት አለመግባባት ቢፈጠር በማን አገር ሕግ፣ በማን ዳኝነት ነው መብቴን የማስከብረው ብሎ ማሰቡ የማይቀር ነው፡፡ በሌላ አገር ተከራክሮ መብቱን የሚያስከብርለት የግልግል ዳኝነት ውሳኔ ቢያገኝ እንኳ፣ የፍርድ ባለዕዳው ሀብት ባለበት አገር የሚገኝ ፍርድ ቤት ለባለመብቱ በሌላ አገር የተሰጠውን የግልግል ውሳኔ ካልተቀበለ እና ካላስፈፀመለት ውሳኔው በራሱ ዋጋ የለውም፡፡ የኒው ዮርክ የግልግል ዳኝነት ስምምነት ይህን ችግር የሚፈታ ነው፡፡

# 1. የኒው ዮርክ ስምምነትን ማጽደቅ ጥቅምና ጉዳት

ከተፈረመ ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ የሆነውን የኒው ዮርክ ስምምነት ቀድመው ከፈረሙት አገራት ውስጥ አንዷ ኢትዮጵያ ብትሆንም እስከ አሁን አላጸደቀችውም፤ በመሆኑም ስምምነቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጻሚ አይደለም፡፡ መንግሥት ይህን ስምምነት እንዲያጸድቅ ተደጋጋሚ ጥያቄዎች በተለይ ከግሉ ሴክተር ቢቀርብለትም እስከ አሁን ስምምነቱ አልፀደቀም፡፡ እንደ ማንኛውም ዓለም ዓቀፍ ስምምነት ይህን ስምምነት ማፅደቁ የራሱ ጥቅምና ጉዳት ቢኖረውም በመንግሥት በኩል ግን እስከ አሁን በኦፊሴል ደረጃ ስምምነቱ የሚያስከትለው ጉዳት ተተንትኖ የማይፀድቅበት ምክንያት አልተገለፀም፡፡

የዚህን ስምምነት መፅደቅ ጥቅምና ጉዳት ከሌሎች አገሮች ተሞክሮ፣ ከዓለም ዓቀፍ ንግድና ኢንቨስትመንት ፍሰት ባህሪይ፣ እንዲሁም ከኢትዮጵያ ሁኔታ በመነሳት እንደሚተከተለው ማጤን ይቻላል፡፡

## 1.1- ስምምነቱን መፈረም የሚያስገኘው ጥቅም

ስምምነቱን መፈረም ብዙ ጥቅም ያስገኛል፡፡ ከብዙዎቹ ጥቅሞች መካከል ጥቂቱን እንደሚከተለው መጥቀስ ይቻላል፡፡

ሀ) ስምምነቱን ማጽደቅ አንድ አገር የውጭ አገር ዜጎች የሚገቡበትን ውል ለመፈፀም ያላትን ቁርጠኝነት ለዓለም ስለሚያሳይ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ያላትን መልካም ስምና ዝና ያሳድጋል፡፡ ይህም የውጭ አንቨስትመንት ፍሰት እንዲጨምር፣ ኤክስፖርት እንዲያድግ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲሳለጥ በማድረግ ስምምነቱ በተዘዋዋሪ (ነገር ግን በአስተማማኝነት) ለኢኮኖሚ ዕድገት፣ ለሥራ ዕድል መስፋፋት እና ለዜጎች ገቢ መጨመር አዎንታዊ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡[1]

ለ) የዓለም ዓቀፍ አበዳሪዎችና ኢንቨስተሮች የሚጠይቁት ወለድ እና ትርፍ ምጣኔ (rate of return) እንዲቀንስ ስምምነቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡ በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ቦንድ በመሸጥ ብድር እየወሰደች መሆኑ

[1] Daniel Berkowitz, Johannes Moenius and Katharina Pistor (2005) “Legal Institutions and International Trade Flows”, *Michigan Journal of International Law*, Vol. 26.

ሲታይ የዚህን ብድር ወለድ ከሚወስኑ ነገሮች አንዱ በዕዳው መክፈል ረገድ ያለው የስጋት (risk) መጠን ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣ በኢትዮጵያ ኩባንያዎች ውስጥ መዋዕለ ነዋይ የሚያፈሱ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ በማንኛውም ዘርፍ ካፒታላቸውን የሚያፈሱ ባለሀብቶች የሚጠብቁት የትርፍ ምጣኔ በኢንቨስትመንቱ ተግባራዊነት ሂደት በተጓዳኝ ከሚገምቱት የስጋት ግዝፈት ወይም አነስተኛነት ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ የኒው ዮርክ ስምምነትን ባፀደቀች አገር ውስጥ የውል አለመፈጸም ስጋት ስለሚቀንስ አበዳሪዎች በአነስተኛ ወለድ እንዲያበድሩ፣ ኢንቨስተሮችም በዝቅተኛ የትርፍ ምጣኔ መዋዕለ ነዋያቸውን እንዲያፈሱ አመቺ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡[2]

ሐ) ስምምነቱን የማጽደቅ ሦስተኛ ጥቅም፣ ስምምነቱን ባፀደቁ ሌሎች አገሮች ውስጥ የኢትዮጵያ ነጋዴዎች ውሎቻቸውን እንዲያስፈጽሙ የሚያስችል መሆኑ ነው፡፡ ይህ በሁለት መልክ የሚገለጽ ነው፡፡ በአንድ በኩል ኢትዮጵያ ስምምነቱን ባለማፅደቋ ምክንያት አብዛኛው የውጭ አገር ነጋዴ ከኢትዮጵያውያን ጋር ሲዋዋል የግልግል ዳኝነት ስምምነቱን ባፀደቀ ሌላ አገር እንዲሆን እያስገደደ ሲሆን፣ ኢትዮጵያ ስምምነቱን ካፀደቀች ግን በኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረግ የግልግል ዳኝነትን ለመቀበል አያቅማማም፡፡ ይህም በተለይ ለአነስተኛ ነጋዴዎች ትልቅ ዕፎይታ ነው፡፡ ቀደም ሲል ፓሪስ ወይም ለንደን ሄዶ ለመከራከር አቅም ያልነበረው ቢያንስ በሀገሩ በሚደረግ የግልግል ዳኝነት መቅረብ አያቅተውም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያ ስምምነቱን ባለማፅደቋ ምክንያት በኢትዮጵያ ውስጥ የተሰጠ ግልግል ዳኝነት ውሳኔን የማይቀበሉ አገሮች ስምምነቱን ኢትዮጵያ ስታጸድቅ አቋማቸው ይቀየራል፡፡ በመሆኑም ኢትዮጵያ ውስጥ የተሰጠን የግልግል ዳኝነት በ150 አገሮች ውስጥ በሚገኝ በማንኛውም የፍርድ ባለዕዳው ሀብት ላይ ማስፈጸም ይቻላል፡፡ ይህ ለኢትዮጵያ ነጋዴዎች ትልቅ መፍትሔ የሚሰጥ ነው፡፡

መ) የውጭ ኢንቬስተሮች እና ነጋዴዎች ከአገራቸው ከመውጣታቸው በፊት በየትኛው አገር ወይም ከየትኛው አገር ነጋዴ ጋር መሥራት እንዳባቸው ከመወሰናቸው በፊት ብዙ አገሮችን ያነፃፅራሉ፡፡ በምርጫቸው ሂደት ከሚያጤኑት መመዘኛ ውስጥ አንዱ አለመግባባት ቢከሰት የሚፈታበት አስተማማኝ ሥርዓት መኖር አለመኖሩ፣ እንዲሁም የሚገቡበት ውል የሚከበር መሆን አለመሆኑ ነው፡፡ ለምሳሌ ወደ ምሥራቅ አፍሪካ ለመምጣት ያሰበ አንድ ኢንቨስተር ይህ መመዘኛ ከኢትጵያ ይልቅ ጎረቤቶቿን እንዲመርጥ ሊያደርገው ይችላል፡፡

አገራችን ስምምነቱን ባታፀድቅም ጥሩ የኢንቨስትመንት ፍሰት ስላላት ይህ ክርክር አሳማኝ ላይመስል ይችላል፡፡ ነገር ግን ስምምነቱን ብትፈርም ከዚህም ይልቅ የበለጠ የውጭ እንቨትመንት ፍሰት ይኖረን እንደነበር አያጠራጥርም፡፡ በሌላ በኩል ይህን በቀላሉ የውጭ ኢንቨስተሮች ለመሳብ የሚያስችል ሥርዓት ባለመጠቀማችን ምክንያት ወደ አገራችን ለመምጣት የሚያመነቱ ኢንቨስተሮችን ለመሳብ በተዘዋዋሪ የምንከፍለው ዋጋ ቀላል ላይሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ ውድ መሬታችንን በአነስተኛ የኪራይ ዋጋ በመስጠት፣ የተጋነነ የታክስ እፎይታ እና ማበረታቻ በመስጠት ወዘተ. ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ከመሞከር ይልቅ ስምምነቱን በማፅደቅ የኢንቨስትመንትን ፍሰት ማጎልበት ይቻላል፡፡

---

2 ዝኒ ከማሁ፡፡

### 1.2- ስምምነቱን መፈረም የሚያስከትለው ጉዳት

የኒው ዮርክ ስምምነት ብዙ ጉዳት የሚያስከትል ሥርዓት አለመሆኑን በተዘዋዋሪ ከሌሎች ተነፃፃሪ ሠነዶች ጋር በማወዳደር ማየት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ እስከ አሁን ስምምነቱን አፅድቀው ተግባራዊ ካደረጉ 150 አገሮች መካከል አንዳቸውም ስምምነቱን አልሻሩም፣ ወይም ከስምምነቱ አልወጡም፡፡ ከኒው ዮርክ ስምምነት ጋር የዓላማ ቅርበት ያለውንና በተቀራራቢ ጊዜ ለፊርማ የቀረበውን በኢንቨስተር እና በኢንቨስትመንት ተቀባይ አገር መካከል የኢንቨስትመንት ያለመግባባትን ለመፍታት የተደረገ የዓለም ዓቀፍ ስምምነት (ICSID Convention) በንፅፅር መመልከት ይቻላል፡፡ ይህ ስምምነት በተለምዶ የዋሽንግተን ስምምነት እየተባለ የሚጠራ ሲሆን፣ ብዙ አገሮች ቢያፀድቁትም አንዳንዶቹ ጉዳቱ እያመዘነባቸው ከስምምነቱ እየወጡ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ከላቲን አሜሪካ አርጀንቲና[3]፣ ቬኔዟላ[4]፣ ኢኳዶር[5] እና ሌሎችንም ስምምነቱን እየተዉ ወትተዋል፡፡ ከዚህ አንፃር የኒው ዮርክ ስምምነትን አልፈልግም ብሎ የወጣ አለመኖሩ ስምምነቱን ማፅደቅ ጉልህ ችግር እንደማያስከትል አመላካች ነው፡፡

ይህ ማለት ግን ስምምነቱን ማፅደቅ ምንም ጉዳት የሌለውና ጥቅም ብቻ የሚያስገኝ ነው ተብሎ ሊወሰድ የሚያስችል አይደለም፡፡ ያም ሆኖ ግን፣ ጥቅሙና ጉዳቱ ሲመዘን ጥቅሙ ይበልጣል ማለት ይቻላል፡፡ የሚከተሉት ሁለት ነጥቦች እንደ ዋና ዋና ጉዳቶች የሚታዩ ናቸው፡፡

ሀ) እንደ ጉዳት ሊታዩ ከሚችሉት ነጥቦች መካከል አንዱ የኒው ዮርክ ስምምነት በሉዓላዊነት ላይ የሚፈጥረው ተጽዕኖ ነው፡፡ አገሮች ማንኛውም ስምምነት ውስጥ ሲገቡ ሉዓላዊነታቸው ላይ ተፅዕኖ እንደሚኖረው ይታመናል፡፡ የኒው ዮርክ ስምምነትም፣ በተለይ በዳኝነት ሉዓላዊነት ላይ ይኸው ባህርይ አለው፡፡ ስምምነቱን ያፀደቀ አገር ፍርድ ቤት በሌላ የስምምነቱ አፅዳቂ አገር የተሰጠን የግልግል ዳኝነት ውሳኔ ተቀብሎ ለማስፈጸም ይገዳዳል፡፡ አልፈጽምም ማለት የሚችለው በሁለት ምክንያቶች ሲሆን፣ እነሱርም ጉዳዩ በአገሩ በግልግል ዳኝነት ለመታየት የማይቻል ከሆነና ውሳኔውን መቀበልም ሆነ ማስፈጸም ከአገሩ ፐብሊክ ፖሊሲ ጋር የሚጣረስ ሆኖ ከተገኘ ነው፡፡ ይህ እንግዲህ የፍርድ ባለዕዳው ውሳኔው እንደይፈጸም ከሚያቀርባቸው ውሱን ምክንያቶች ውጭ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ስምምነቱን ባፀደቀች አገር ውስጥ የሚገኝ የግልግል ዳኛ የሚሰጠው ውሳኔ አምስት ዳኞች የሚሰጡትን የሰበር ውሳኔ ያህል የጸና ነው ለማለት ይቻላል፡፡ በስምምነቱ ውስጥ በተቀመጡት ውሱን ምክንያቶች ካልሆነ በቀር ውሳኔውን ከመፈጸም ውጭ አማራጭ የለም፡፡

ለ) ሌላው እንደ ጉዳት ሊታይ የሚችለው ስምምነቱን ማፅደቅ የኢትዮጵያ ነጋዴዎች ዓለም ዓቀፍ ውሎችን ላለመፈጸም ያላቸውን አማራጭ ማስቀረቱ ነው፡፡ ከሞራል አኳያ ይህን ጥቅም እንደ ልዩ ጥቅም ማንሳት አግባብነት የሌለው ቢሆንም፣

[3] Oscar Lopez, Smart Move: Argentina Leaves ICSID: Cornell International Journal Online, available at < http://cornellilj.org/smart-move-argentina-to-leave-the-icsid> viewed on 20 December 2014.

[4] Available at < https://www.iisd.org/itn/2012/04/13/venezuelas-withdrawal-from-icsid-what-it-does-and-does-not-achieve/> , viewed on 20 December 2014.

[5] Available at < http://www.iareporter.com/articles/EcuadorExit>, viewed on 20 December 2014.

ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙ ሲታይ ግን የተወሰነ ትኩረት የሚሰጠው አማራጭ ነው፡፡ አንዳንዴ ውሎችን አለመፈጸም ጠቃሚ የሚሆንበት እውነታ ሊያጋጥም ይችላል፡፡ ኢትዮጵያ ስምምነቱን ስታጸድቅ የየትኛውም አገር የፍርድ ባለመብት በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ቀርቦ በኢትዮጵያ ባለ የፍርድ ባለዕዳው ንብረት ላይ ፍርዱን እንዲያስፈፅም የኒው ዮርክ ስምምነት የሚያስችል በመሆኑ ይህን የመሰለውን ክፍተት መጠቀም የሚፈልጉ ነጋዴዎች ለግልግል ዳኝነት አፈጻጸም ይጋለጣሉ፡፡

እንግዲህ እነዚህ ጥቅሞችና ጉዳቶች ሲነፃፀሩ ስምምነቱን ማፅደቅ ከጉዳቱ ጥቅሙ እንደሚያመዝን ይታያል፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ መንግሥት ይህን ስምምነት ማፅደቅ ይጠበቅበታል፡፡

## 2. የስምምነቱ አጠቃላይ ይዘት ጠቅለል ያለ ዕይታ

ስምምነቱ በአጠቃላይ 16 አንቀጾች ያሉት ሲሆን በፈራሚ አገሮች ላይ ሁለት ዋና ዋና ግዴታዎችን ይጥላል፡፡ የመጀመሪያው ዐብይ ግዴታ፣ በውጭ አገር ለተሰጡ የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች እውቅና የመስጠትና እነዚህን ውሳኔዎች የመፈፀም ግዴታ ሲሆን፤ ሁለተኛው ግዴታ ደግሞ፣ የፈራሚ አገር ፍርድ ቤቶች የግልግል ስምምነት ያረፈባቸው ክርክሮች በቀረቡላቸው ጊዜ ተከራካሪዎቹን ወደ ግልግል ዳኝነት እንዲመሩ የሚጠይቅ ነው፡፡[6]

### ሀ) የውጭ አገር የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎችን የማወቅና የመፈፀም ግዴታ

በስምምነቱ አንቀጽ 1 መሠረት ‹‹የውጭ አገር የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች›› በሚለው አገላለጽ የሚያሳየው ውሳኔው እንዲታወቅ እና እንዲፈጸም አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት ከሚገኝበት አገር ውጭ የተሰጠ ውሳኔ መሆን እንዳለበት ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ፈራሚ አገሮች የውጭ አገር የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎችን በየአገራቸው የሥነ-ሥርዓት ሕግ መሠረት እውቅና እንዲሰጡና እንዲያስፈጽሙ አንቀጽ 3 ይደነግጋል፡፡ በውጭ አገር የተሰጠ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ እንዲፈጸምለት የሚጠይቅ አመልካች ክርክሩን ለግልግል ዳኝነት ለማቅረብ የተስማማበትን የግልግል ስምምነት እና የግልግል ዳኝነት ውሳኔውን ኮፒዎች ለፍርድ ቤቱ ማቅረብ እንዳለበት በስምምነቱ አንቀጽ 4 ተደንግጓል፡፡

በተቃራኒው በውጭ አገር የተሰጠው የግልግል ዳኝነት ውሳኔ እውቅና ሊያገኝና ሊፈጸም አይገባውም የሚለው ወገን (የፍርድ ባለዕዳው) ሊያቀርብ የሚችላቸው የተወሰኑ ምክንያቶች በአንቀጽ 5 ተመልክተዋል፡፡ በውጭ አገር የተሰጠ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ እንዲፈጸም የቀረበን ማመልከቻ ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነት አልቀበልም ለማለት የሚችልባቸው ምክንያቶችም በዚሁ አንቀጽ 5(2) ላይ ተገልፀዋል፡፡ የግልግል ዳኝነት ውሳኔው በተሰጠበት አገር (ማለትም በውሳኔው መነሻ አገር) ፍርድ ቤት ውስጥ ውሳኔው እንዲሻር አሊያም እንዲሰረዝ ማመልከቻ መቅረቡን ይኸው የቀረበለት አገር ፍርድ ቤት የተረዳ እንደሆነ በማመልከቻው ላይ የሚሰጠውን ወሳኔ በአንቀጽ 6 መሠረት በቀጠሮ ማስተላለፍና የውሳኔውን መነሻ አገር ፍርድ ቤት ውሳኔ መጠበቅ

[6] Albert Jan van den Berg, The New York Convention of 1958: An Overview, available < http://www.arbitration-icca.org/media/0/12125884227980/new_york_convention_of_1958_overview.pdf> , viewed on 20 December 2014

ይችላል፡፡ በውጭ አገር የተሰጠ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ እንዲፈጸም የሚጠይቀው አመልካች በሚያቀርበው ማመልከቻ ጥያቄውን ባቀረበበት አገር የውስጥ ሕግ (domestic law) ወይም በሌላ ዓለም ዓቀፍ ስምምነት መሠረት እንዲፈፀምለት ለመጠየቅ እንደሚችል አንቀጽ 7 ይደነግጋል፡፡ ይህም አመልካቹ የተሻለውን የሕግ (the more favorable right) መምረጥ እንደሚችል አመላካች ነው፡፡

**ለ) ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ክርክሩን ወደግልግል ለመምራት የተጣለበት ግዴታ**

ተከራካሪዎች በግልግል ዳኝነት ለመፍታት የተስማሙበትን አንድ ጉዳይ ወደ ፍርድ ቤት በወሰዱ ጊዜ (አንዱ ወገን ሲያመለክት) የስምምነነቱ ፈራሚ አገር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ወደ ግልግል ዳኝነት እንዲሄድ ማድረግ እንዳለባቸው በአንቀጽ 2(3) ተደንግጓል፡፡ ይህም የግልግል ዳኝነትን የማበረታታት ዓላማ አለው፡፡

**ሐ) የሁለቱ ግዴታዎች ትግበራ ሥነሥርዓቶችና የስምምነቱ ጥቅም**

ከላይ በተራ ቁጥር ሀ እና ለ የተመለከቱት ግዴታዎች ተግባራዊ ይሆኑ ዘንድ በኒው ዮርክ ስምምነት መሠረት ተቀባይነት ያለው የግልግል ስምምነት ውል መቅረብ ይኖርበታል፡፡ የግልግል ስምምነቱ (ውሉ) በጽሁፍ መሆን ያለበት ቢሆንም ‹‹ጽሁፍ›› የሚለው ቃል የግድ ምስክሮች ባሉበት ወይም በውል አዋዋይ ፊት ተደረገ ብቻ ለማለት ሳይሆን በማንኛውም የተጻፈ ሠነድ የተደገፈ ለማለት ተስቦ የገባ መሆኑን ከስምምነቱ አንቀጾች መረዳት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ ስምምነቱ የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ተቀባይነት እንዲኖራቸው በማድረጉ ለዓለም ዓቀፍ ንግድና ኢንቨስትመንት መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ እዚህ ላይ ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ጉዳይ የኒው ዮርክ ስምምነት በራሱ በአንድ አገር ውስጥ ጥሩ የግልግል ሕግና ሥርዓት እንዲኖር ያስችላል ማለት አይደለም፡፡ ስምምነቱ የሚመለከተው በውጭ አገር የተሰጡ የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎችን ተቀባይነት ማረጋገጥና አፈፃፀም ብቻ ነው፡፡ የአንድ አገር የግልግል ዳኝነት ሕግ ምን መምሰል አለበት የሚለውን ጉዳይ የኒው ዮርክ ስምምነት አይመለከትም፡፡ ስለሆነም በአንድ አገር ውስጥ ቀልጣፋ፣ ርትዐዊና ውጤታማ የግልግል ዳኝነት ሥርዓት እንዲፈጠር ስምምነቱን ከማፅደቅ በተጨማሪ ጥሩ የግልግል ዳኝነት ሕግ፣ ነፃና ገለልተኛ እንዲሁም ከሙስና የፀዳ ፍርድ ቤት መኖር አለበት፡፡

## 3. ስምምነቱን ከማጽደቅ አንጻር የኢትዮጵያ ቀጣይ እርምጃ ምን መሆን አለበት

ኢትዮጵያ በአፍሪካ የንግድና ኢንቨስትመንት ማዕከል ለመሆን ቁርጠኝነቷን እየገለፀች ከመሆኗ አኳያ፣ ስምምነቱን በቀዳሚነት ከፈረሙት አገሮች አንዷ እንደመሆኗ፣ እንዲሁም በሁለት አሥርት ዓመታት ውስጥ ኢኮኖሚዋን በእጅጉ በማሳደግ በግሉ ዘርፍ ሞተርነት መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተራ የመሰለፍ ግቧን ከመግለጧ አንፃር፣ ለዓለም ዓቀፍ ንግድና ኢንቨስትመንት መሠረት ከሆኑት አመቺ ሁኔታዎች መካከል አንዱ የሆነውን ይህን ስምምነት ማፅደቋ ላስቀመጠቻቸው ግቦች መሳካት ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ ይህም ለዜጎቿ የሚሰጠው ጥቅም፣ ሊያስከትል ይችላል ተብሎ ከሚታሰበው ጉዳት እጅግ የላቀ ነው፡፡ ■

# አባሪ (Annex)

## በተባበሩት መንግሥታት የዓለም-ዓቀፍ የንግድ ግልግል ዳኝነት ጉባኤ

## በውጭ አገር የተሰጡ የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች እውቅናና አፈጻጸም ላይ የተደረገ ስምምነት

**የተባበሩት መንግሥታት 1950 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ. 1958)**

### በውጭ አገር የተሰጡ የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች እውቅናና አፈጻጸም ስምምነት[7]

### አንቀጽ 1

1. ይህ ስምምነት እውቅና እና አፈጻጸም ከተጠየቀበት አገር ግዛት ውጭ የሕግ ወይም የተፈጥሮ ሰውነት ባላቸው ሰዎች መካከል በሚነሱ አለመግባባቶች ላይ በሚሰጡ የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች ተፈጻሚ ይሆናል። የግልግል ዳኝነት ውሳኔው እውቅና አፈጻጸም በተጠየቀበት አገር ውስጥ የተሰጠ እንኳ ቢሆን የዚያው አገር ውስጥ ውሳኔ ነው ተብሎ የማይቆጠር ከሆነ ስምምነቱ ተፈጻሚ ይሆናል።

2. ‹የግልግል ዳኝነት ውሳኔ› የሚለው ሐረግ ለእያንዳንዱ ጉዳይ በተናጠል የተሾሙ የግልግል ዳኞች ከሚሰጡት ውሳኔ በተጨማሪ ተከራካሪ ወገኖቹ በሰየሚቸው ቋሚ የግልግል ዳኝነት አካላት የሚሰጡ ውሳኔዎችንም ያካትታል።

3. ማንኛውም መንግሥት ይህን ስምምነት ሲፈርም፣ ሲያፀድቅ፣ ወይም ወደ ስምምነቱ ኋላ ሲቀላቀል፣ አሊያም በአንቀጽ 10 መሠረት በሚያስተዳድራቸው ግዛቶች ውስጥ የስምምነቱን ተፈጻሚነት ሲያሳውቅ በእንካ-ለእንካ መርሆ መሠረት ስምምነቱን የሚፈጽመው በሌላ የስምምነቱ ተፈራራሚ መንግሥት ግዛት ውስጥ ለተሰጡ የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች ብቻ ነው ሲል ማሳወቅ ይችላል። በተመሳሳይ ሁኔታ ይኸው መንግሥት ስምምነቱን የምፈጽመው በራሴ ሕግ መሠረት የንግድ ለሆኑ ከውል ወይም ከውል ውጭ ከሚፈጠሩ ሕጋዊ ግንኙነቶች በሚመነጩ አለመግባባቶች ላይ ብቻ ነው ብሎ ማሳወቅ ይችላል።

### CONVENTION ON THE RECOGNITION AND ENFORCEMENT OF FOREIGN ARBITRAL AWARDS

### Article I

1. This Convention shall apply to the recognition and enforcement of arbitral awards made in the territory of a State other than the State where the recognition and enforcement of such awards are sought, and arising out of differences between persons, whether physical or legal. It shall also apply to arbitral awards not considered as domestic awards in the State where their recognition and enforcement are sought.

2. The term “arbitral awards" shall include not only awards made by arbitrators appointed for each case hut also those made by permanent arbitral bodies to which the parties have submitted.

3. When signing, ratifying or acceding to this Convention, or notifying extension under article X hereof, any State may on the basis of reciprocity declare that it will apply the Convention to the recognition and enforcement of awards made only in the territory of another Contracting State. It may also declare that it will apply the Convention only to differences arising out of legal relationships, whether contractual or not, which are considered as commercial under the national law

---

[7] ትርጉም፣ ፈቃዱ ጴጥሮስ ገ/መስቀል

### አንቀጽ 2

1. እያንዳንዱ የስምምነቱ አባል መንግሥት በተዋዋዮች ከውል ወይም ከውል ውጭ የተፈጠሩ ወይም ከአንድ ሕጋዊ ግንኙነት ሊነሱ የሚችሉ ማናቸውም በግልግል ዳኝነት ሊፈቱ የሚችሉ ያለመግባባቶችን በከፊል ወይም በሙሉ ለግልግል ዳኝነት ለማቅረብ በጽሁፍ የተደረገን ስምምነት ይቀበላል፡፡
2. "በጽሁፍ የተደረገ ስምምነት" የሚለው ሐረግ በተዋዋዮች የተፈረመ ወይም ባደረጓቸው የደብዳቤ አሊያም የቴሌግራም ልውውጦች የተካተተ ሆኖ በውል ውስጥ የሰፈረ የግልግል አንቀጽ ወይም ለብቻው ራሱን ችሎ የተደረገ የግልግል ስምምነትን ያጠቃልላል፡፡
3. የግልግል ስምምነቱ ፈራሽ እና ዋጋ የሌለው፣ የማይሠራ ወይም ሊፈጸም የማይችል ካልሆነ በስተቀር የአባል መንግሥት ፍርድ ቤት ከላይ በተገለፀው አግባብ የግልግል ስምምነት የተደረገለት ጉዳይ በቀረበለት ጊዜ፣ እና ከተዋዋዮቹ አንዱ ሲጠይቅ፣ ጉዳዩን ወደ ግልግል ዳኝነት ይመራል፡፡

### አንቀጽ 3

እያንዳንዱ አባል መንግሥት በአገሩ ባለው የሥነ-ሥርዓት ሕግ መሠረትና ከዚህ ቀጥለው በሰፈሩት ሁኔታዎች አግባብ ለግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች እውቅና ይሰጣል፤ ይፈጽማል፡፡ በመሆኑም ለአገር ውስጥ የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች ከሚሰጠው እውቅና እና አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር በዚህ ስምምነት ለሚሸፈኑት የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች የሚሰጥ እውቅናና አፈጻጸምን በተመለከተ የከበደ ሥርዓት መዘርጋት፣ ወይም ከፍተኛ የአገልግሎት ወይም አስተዳደራዊ ወጪ ማስከፈል አይቻልም፡፡

### አንቀጽ 4

1. ከዚህ በላይ በተመለከተው አንቀጽ መሠረት የግልግል ዳኝነት ውሳኔ እንዲፈጸምለት የሚጠይቅ ወገን ማመልከቻውን በሚያቀርብበት ጊዜ የሚከተሉትን ሠነዶች ማካተት አለበት፡-
   ሀ. በአግባቡ የተረጋገጠውን ዋናውን ውሳኔ እና የተመሳከረ ቅጂ፤
   ለ. በአንቀጽ 2 የተገለጸውን ስምምነት ዋናውን ወይም የተመሳከረ ቅጂ፡፡
2. የግልግል ውሳኔው ወይም ስምምነቱ እንዲፈጸም በተጠየቀበት አገር የሥራ ቋንቋ የተደረገ ካልሆነ ውሳኔው እንዲታወቅና እንዲፈጸም የሚጠይቀው አመልካች ሰነዶቹን በአገሩ የሥራ ቋንቋ አስተርጉሞ ማቅረብ አለበት፡፡ የተተረጎመውም ሠነድ በባለሥልጣን፣ በሕጋዊ ተርጓሚ አሊያም በዲፕሎማቲክ ወይም ቆንጽላ ጽ/ቤት መረጋገጥ አለበት፡፡

### አንቀጽ 5

1. የውጭ አገር የግልግል ዳኝነት ውሳኔ እውቅና እንዲያገኝ እና እንዲፈጸም በተጠየቀ ጊዜ ውሳኔው እንዲፈጸምበት የተሰየመው ተጠሪ ለሚመለከተው ባለሥልጣን ውሳኔው እውቅና እንዳያገኝ እና እንዳይፈጸም ካመለከተና በማመልከቻውም የሚከተሉትን ካረጋገጠ ብቻ እውቅናና እና አፈጻጸም ሊከለከል ይችላል፡፡
   ሀ. በአንቀጽ 2 የተጠቀሰውን ስምምነት ያደረጉት ተዋዋዮች በሚገዛቸው ሕግ መሠረት ውል ለማድረግ ችሎታ እንዳልነበራቸው፣ ወይም ተዋዋዮቹ ስምምነቱ እንዲገዛበት በጠቀሱት ሕግ ወይም ይህም ካልታወቀ የግልግል ዳኝነት ውሳኔው በተሰጠበት አገር ሕግ መሠረት ስምምነቱ ፈራሽ እንደሆነ፤
   ለ. ውሳኔው እንዲፈጸምበት የተሰየመው ተጠሪ የግልግል ዳኞቹ ሲሾሙ፣ ወይም የግልግል ዳኝነቱ ሲካሄድ በአግባቡ እንዲያውቅ እንዳልተደረገ፣ አሊያም ክርክሩን በተገቢው መንገድ ለማቅረብ ዕድል እንዳላገኘ፤
   ሐ. ውሳኔው ተዋዋዮቹ ለግልግል ባላቀረቡት ጉዳይ ላይ የተሰጠ እንደሆነ፣ ወይም ለግልግል ካቀረቡት ጉዳይ ውጭ ያሉ ጉዳዮችን እንደሚጨምር፤ ይህም ሲሆን ተዋዋዮቹ ለግልግል ዳኝነት ባቀረቡት ጉዳይ ላይ የተሰጠው የውሳኔው ክፍል ተዋዋዮቹ ለግልግል ያላቀረቡት ጉዳይ ላይ ከተሰጠው ውሳኔ መለየት የሚቻል መሆኑና የቀደመው ውሳኔ ተለይቶ ለብቻው ሊፈጸም እንደሚችል፤
   መ. የግልግል ዳኝነት ጉባኤው ስብጥር ወይም የዳኝነት ሂደቱ በተዋዋዮች ስምምነት መሠረት እንዳልተካሄደ፤ ይህ ዓይነት ስምምነት የሌለ እንደሆነም የግልግል ዳኝነቱ በተካሄደበት አገር ሕግ አግባብ እንዳልተፈጸመ፤
   ሠ. የግልግል ዳኝነት ውሳኔው ገና እንዳልጸና፣ ወይም ውሳኔው በተሰጠበት አገር ወይም ውሳኔው መሠረት ባደረገው አገር፣ አግባብነት ባለው ባለሥልጣን እንደተሰረዘ ወይም እንደታገደ፡፡
2. የግልግል ዳኝነት ውሳኔ እውቅና እንዲያገኝ እና እንዲፈጸም የቀረበለትን ጥያቄ ማስተናገድ የሚችል ባለሥልጣን በሚከተሉት ተጨማሪ ምክንያቶች ማመልከቻውን አልቀበልም ለማለት ይችላል፡፡
   ሀ. ለግልግል የቀረበው ጉዳይ የዕውቅናና አፈጻጸም ማመልከቻ በቀረበበት አገር ሕግ መሠረት በግልግል ዳኝነት ሊታይ የማይችል ከሆነ፣ ወይም
   ለ. የውሳኔው መታወቅ እና መፈጸም ከአገራዊ ፖሊሲ ጋር የሚቃረን ከሆነ፡፡

**Article II**

I. Each Contracting State shall recognize an agreement in writing under which the parties undertake to submit to arbitration all or any differences which have arisen or which may arise between them in respect of a defined legal relationship, whether contractual or not, concerning a subject matter capable of settlement by arbitration.

2. The term “agreement in writing" shall include an arbitral clause in a contract or an arbitration agreement, signed by the parties or contained in an exchange of letters or telegrams.

3. The court of a Contracting State, when seized of an action in a matter in respect of which the parties have made an agreement within the meaning of this article, shall, at the request of one of the parties, refer the parties to arbitration, unless it finds that the said agreement is null and void, inoperative or incapable of being performed.

**Article III**

Each Contracting State shall recognize arbitral awards as binding and enforce them in accordance with the rules of procedure of the territory where the award is relied upon, under the conditions laid down in the following articles. There shall not be imposed substantially more onerous conditions or higher fees or charges on the recognition or enforcement of arbitral awards to which this Convention applies than are imposed on the recognition or enforcement of domestic arbitral awards.

**Article IV**

l. To obtain the recognition and enforcement mentioned in the preceding article, the party applying for recognition and enforcement shall, at the time of the application, supply:

(a) The duly authenticated original award or a duly certified copy thereof;

(b) The original agreement referred to in Article 11 or a duly certified copy thereof.

2. If the said award or agreement is not made in an official language of the country in which the award is relied upon, the party applying for recognition and enforcement of the award shall produce a translation of these documents into such language. The translation shall be certified by an official or sworn translator or by a diplomatic or consular agent.

**Article V**

1. Recognition and enforcement of the award may be refused, at the request of the party against whom it is invoked, only if that party furnishes to the competent authority where the recognition and enforcement is sought, proof that:

(a) The parties to the agreement referred to in article II were, under the law applicable to them under some incapacity, or the said agreement is not valid under the law to which the parties have subjected it or, failing any indication thereon, under the law of the country where the award was made; or

(b) The party against whom the award is Invoked was not given proper notice of the appointment of the arbitrator or of the arbitration proceedings, or was otherwise unable to present his case, or

(c) The award deals with a difference not contemplated by, or not falling within the terms of the submission to arbitration, or it contains decisions on matters beyond the scope of the submission to arbitration; provided that if the decision on matters submitted to arbitration can be separated from those not so submitted, that part of the award which contains decisions on matters submitted to arbitration may be recognized and enforced; or

(d) The composition of the arbitral authority or the arbitral procedure was not in accordance with the agreement of the parties, or, failing such agreement, was not in accordance with the law of the country where the arbitration took place; or

(e) The award has not yet become binding on the parties, or has been set aside or suspended by a competent authority of the country in which, or under the law of which, that award was made.

2. Recognition and enforcement of an arbitral award may also be refused if the competent authority in the country where recognition and enforcement is sought finds that:

(a) The subject matter of the difference is not capable of settlement by arbitration under the law of that country; or

(b) The recognition or enforcement of the award would be contrary to the public policy of that country.

### አንቀጽ 6

የግልግል ዳኝነት ውሳኔ እንዲታወቅና እንዲፈጸም ማመልከቻ የቀረበለት አካል ውሳኔው እንዲሰረዝ ወይም እንዲታገድ በአንቀጽ 5(1)(ሠ) መሠረት ለተጠቀሰው አካል ማመልከቻ መቅረቡን ካወቀና ተገቢ መስሎ ከታየው የማሰረዝ ወይም የማሳገድ ማመልከቻው ላይ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ የጊዜ ቀጠሮ ሊሰጥ ይችላል፣ በተጨማሪም ውሳኔው እውቅና እንዲያገኝና እንዲፈጸም ያመለከተው ወገን ከጠየቀ ሌላው ወገን ተገቢውን መያዣ እንዲያስይዝ ለማዘዝ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 7

1. የዚህ ስምምነት ድንጋጌዎች በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ፈራሚ መንግሥታት መካከል የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎችን እውቅናና አፈጻጸም በተመለከተ፣ የሚደረጉ ስምምነቶችን ሊሽር ወይም በእነዚህ ስምምነቶች ወይም ሌላ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት እና ልክ ማኛኛውም ከግልግል ዳኝነት ውሳኔ መብት አለኝ የሚል አመልካች ሊኖረው የሚችልን ማንኛውም መብት አያሳጣውም፡፡
2. በዚህ ስምምነት አድራጊ መንግሥታት መካከል ቀደም ሲል የተደረጉት የእ.ኤ.አ. 1916 የጀኔቫ የግልግል ዳኝነት አንቀጾች ፕሮቶኮል እና የእ.ኤ.አ 1920 የጀኔቫ የውጭ አገር የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች አፈጻጸም ስምምነት ይህ ስምምነት በሥራ በዋለበት ጊዜና ደረጃ ተሽረዋል፡፡

### አንቀጽ 8

1. ይህ ስምምነት ለማንኛውም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል፣ ወይም ለየትኛውም ለተባበሩት መንግሥታት ልዩ ተቋማት ነባር አባል ወይም የወደፊት አባል፣ ወይም ለየትኛውም የዓለም-አቀፍ ፍርድ ቤት መመሥረቻ ሕግ ነባር ወይም የወደፊት ፈራሚ መንግሥት፣ ወይም ለየትኛውም የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ የአባልነት ግብዣ ለሚልክለት መንግሥት እንዲፈርሙበት እ.ኤ.አ. እስከ ዲሴምበር 31 1958 ድረስ ክፍት ሆኖ ይቆያል፡፡
2. ስምምነቱ መጽደቅ ያለበት ሲሆን የጸደቀበት ማስረጃ በተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ ዘንድ መቀመጥ አለበት፡፡

### አንቀጽ 9

1. ይህ ስምምነት ለሁሉም በአንቀጽ 8 ለተመለከቱት አገሮች ኋላ እንዲቀላቀሉበት ክፍት ሆኖ ይቆያል፡፡
2. ኋላ መቀላቀል የሚፈጸመው የመቀላቀል ውሳኔ ሠነድ በተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ ዘንድ በማስቀመጥ ይሆናል፡፡

### አንቀጽ 10

1. ማንኛውም መንግሥት ይህን ስምምነት ሲፈርም፣ ሲያጸድቅ ወይም ወደ ስምምነቱ ኋላ ሲቀላቀል ስምምነቱን በሁሉም የዓለም-አቀፍ ግንኙነታቸውን በሚመራላቸው ግዛቶች ውስጥ ወይም ከእነዚህ በተወሰኑት ውስጥ ብቻ እንደሚፈጽመው ሊያሳውቅ ይችላል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ማስታወቂያ ውጤት የሚኖረው ስምምነቱ እውቅና በሚሰጠው መንግሥት አገር ውስጥ ሥራ ላይ ከሚውልበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡
2. ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ማንኛውም ስምምነቱ የሚፈጸምበትን የግዛት ወሰን የማስፋፋት ውሳኔ ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ በሚላክ ማስታወቂያ የሚደረግ ሆኖ፣ ስምምነቱ በተባለው ግዛት ተፈጻሚ መሆን የሚጀምረው ማስታወቂያ ለዋና ጸሐፊው ከደረሰበት ቀን አንስቶ በሚቆጠር ዘጠና ቀንና በአገሩ ውስጥ ስምምነቱ ተፈጻሚ በሚሆንበት ቀን መካከል ቀድሞ ከሚደርሰው ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡
3. ይህን ስምምነት በሚፈርሙበት፣ በሚያጸድቁበት አሊያም አገሮች ስምምነቱን ኋላ በሚቀላቀሉበት ጊዜ ስምምነቱ ያልተስፋፋባቸውን ግዛቶች በተመለከተ፣ እያንዳንዱ የሚመለከተው ተፈራራሚ መንግሥት ስምምነቱ ያልተስፋፋበትን ግዛት አስተዳደር ፍላጎት እና ሕገ-መንግሥት በጠበቀ መልኩ ስምምነቱ ወደዚሁ ግዛት እንዲስፋፋ አዎንታዊ ጥረት ማድረግ አለበት፡፡

**Article VI**

If an application for the setting aside or suspension of the award has been made to a competent authority referred to in article V (l) *(e),* the authority before which the award is sought to be relied upon may, if it considers it proper, adjourn the decision on the enforcement of the award and may also, on the application of the party claiming enforcement of the award, order the other party to give suitable security

**Article VII**

1. The provisions of the present Convention shall not affect the validity of multilateral or bilateral agreements concerning the recognition and enforcement of arbitral awards entered into by the contracting States, nor deprive any interested party of any right he may have to avail himself of an arbitral award in the manner and to the extent allowed by the law or the treaties of the country where such award is sought to be relied upon.
2. The Geneva Protocol on Arbitration Clauses of 1923 and the Geneva Convention On the Execution of Foreign Arbitral Awards of 1927 shall cease to have effect between Contracting States on their becoming bound and to the extent that they become bound, by this Convention.

**Article VIII**

1. This Convention shall be open until 31 December 1958 for signature on behalf of any Member of the United Nations and also on behalf of any other State which is or hereafter becomes a member of any specialized agency of the United Nations, or which is or hereafter becomes a party to the Statute of the International Court of Justice, or any other State to which an invitation has been addressed by the General Assembly of the United Nations.
2. This Convention shall be ratified and the instrument of ratification shall be deposited with the Secretary-General of the United Nations.

**Article IX**

I. This Convention shall be open for accession to all States referred to in article VIII.

2. Accession shall he effected by the deposit of an instrument of accession with the Secretary General of the United Nations.

**Article X**

1. *Any* State may, at the time of signature, ratification or accession, declare that this Convention shall extend to all or any of the territories for the international relations of which it is responsible. Such a declaration shall take effect when the Convention enters into force for the State concerned.
2. At any time thereafter any such extension shall be made by notification addressed to the Secretary-General of the United Nations and shall take effect as from the ninetieth day after the day of receipt by the Secretary-General of the United Nations of this notification, or as from the date of entry into force of the Convention for the State concerned, whichever is the later.
3. With respect to those territories to which this Convention is not extended at the time of signature, ratification or accession, each State concerned shall consider the possibility of taking the necessary steps in order to extend the application of this Convention to such territories, subject, where necessary for constitutional reasons to the consent of the Governments of such territories.

**አንቀጽ 11**

ፌዴራላዊ ወይም ያልተማከለ አስተዳደር ያላቸውን መንግሥታት በተመለከተ የሚከተሉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

1. በፌዴራሉ መንግሥት የሕግ ማውጣት ሥልጣን ውስጥ የሚወድቁትን የዚህን ስምምነት አንቀጾች በተመለከተ የፌዴራሉ መንግሥት ሌሎች ፌዴራላዊ ያልሆኑ መንግሥታት ያለባቸውን ያህል ግዴታዎች ይኖሩታል፡፡
2. በክልል ወይም በፌዴሬሽኑ አባል ግዛቶች ሕግ የማውጣት ሥልጣን ውስጥ የሚወድቁትን የዚህን ስምምነት አንቀጾች በተመለከተ ክልላዊ መንግሥታቱ በፌዴሬሽኑ ሕገ-መንግሥት መሠረት ሕግ ለማውጣት የማይገደዱ ከሆነ፣ እነዚህን አንቀጾች ክልላዊ መንግሥታት ወደ ሕግነት እንዲቀይሯቸው የፌዴራል መንግሥቱ ምክረ ሓሳብ ያቀርባል፡፡
3. የዚህ ስምምነት አባል የሆነ የፌዴራል መንግሥት ሌሎች አባል መንግሥታት በዋና ጸሐፊው በኩል ጥያቄ ሲያቀርቡ፣ የዚህን ስምምነት አንድ አንቀጽ በተመለከተ ያለውን የፌዴሬሽኑንና የፌዴሬሽኑ አባል መንግሥታትን ሕግ እና የሕጉን አተገባበር እንዲሁም ስምምነቱ ለመፈፀም ያደረገውን ሕግ የማውጣት ወይም ሌላ ተግባር የሚገልድ ማስታወሻ መስጠት አለበት፡፡

**አንቀጽ 12**

1. ይህ ስምምነት ሦስተኛው የማጽደቂያ ወይም ኂላ የመቀላቀል ሠነድ ከተመዘገበበት ቀን አንስቶ በሚቆጠር ከዘጠናኛው ቀን ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል፡፡
2. እያንዳንዱ የዚህ ስምምነት ሦስተኛው የማጽደቂያ ወይም ኂላ የመቀላቀል ሠነድ ከተመዘገበበት ቀን በኂላ ስምምነቱን የሚያጸድቅ ወይም ኂላ የሚቀላቀል መንግሥትን በተመለከተ የማጽደቂያ ወይም ኂላ የመቀላቀል ሠነዱን ካስመዘገበበት ቀን በኂላ ባለው ዘጠናኛ ቀን ስምምነቱ በሥራ ላይ ይውላል፡፡

**አንቀጽ 13**

1. ማንኛውም የዚህ ስምምነት አባል መንግሥት ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ በሚላክ የጽሑፍ ማስታወቂያ ከስምምነቱ መውጣቱን ሊያሳውቅ ይችላል፡፡ ከስምምነት መውጣቱ ውጤት የሚያገኘው ማስታወቂያው ለዋና ጸሐፊ ከደረሰ ከአንድ ዓመት በኂላ ነው፡፡
2. ማንኛውም በአንቀጽ 10 መሠረት መግለጫ ወይም ማስታወቂያ የሰጠ አባል መንግሥት፣ በማንኛውም ጊዜ ቢሆን ለዋና ጸሐፊው በሚላክ ማስታወቂያ ስምምነቱ በሚመለከተው የውጭ ግንኙነቱን በሚመራለት ግዛት ውስጥ ማስተወቂያው ለዋና ጸሐፊ ከደረሰ ከአንድ ዓመት በኂላ ተፈፃሚነቱ እንደሚቋረጥ መግለጫ ሊሰጥ ይችላል፡፡
3. ከአባልነት መውጣቱ ውጤት ከማግኘቱ በፊት እንዲታወቁ ወይም እንዲፈጸሙ ማመልከቻ የቀረበባቸውን የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች በተመለከተ ይህ ስምምነት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 14**

አንድ የዚህ ስምምነት አባል መንግሥት ራሱ ስምምነቱን ለመፈጸም ከገባበት ግዴታ ልክ በላይ ሌሎች አባል መንግሥታት ስምምነቱን እንዲያከብሩለት ሊጠይቅ አይችልም፡፡

**አንቀጽ 15**

የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ በአንቀጽ 8 ሥር ለተጠቀሱት መንግሥታት የሚከተለውን ማስታወቅ አለበት፡፡

ሀ. በአንቀጽ 8 መሠረት የተደረጉ ፊርማዎችንና ማስታወቂያዎችን፤

ለ. በአንቀጽ 9 መሠረት የተፈጸሙ ኂላ መቀላቀሎችን፤

ሐ. በአንቀጽ 1፣10 እና 11 መሠረት የተደረጉ መግለጫዎችንና ማስታወቂያዎችን፤

መ. በአንቀጽ 12 መሠረት ይህ ስምምነት በሥራ የሚውልበትን ቀን፣

ሠ. በአንቀጽ 13 መሠረት የተደረጉ ከስምምነቱ የመውጣት ማስታወቂያዎችንና መግለጫዎችን፡፡

**አንቀጽ 16**

1. ይህ ስምምነት በቻይንኛ፣ በእንግሊዝኛ፣ በፈረንሳይኛ፣ በመስኮብኛ እና በእስፓኝ ቋንቋዎች እኩል ደረጃ ባላቸው ትርጉሞች ታትሞ በተባበሩት መንግሥታት ቤተ መዛግብት ይቀመጣል፡፡
2. የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ በአንቀጽ 8 ለተመለከቱት መንግሥታት የስምምነቱን የተረጋገጠ ግልባጭ ይልካል፡፡

**Article XI**

In the case of a federal or non-unitary State, the following provisions shall apply:

(a) With respect to those articles of this Convention that come within the legislative jurisdiction of the federal authority, the obligations of the federal Government shall to this extent be the same as those of Contracting States which are not federal States;

(b) With respect to those articles of this Convention that come within the legislative jurisdiction of constituent states or provinces which are not, under the constitutional system of the federation, bound to take legislative action, the federal Government shall bring such articles with a favorable recommendation to the notice of the appropriate authorities of constituent states or provinces at the earliest possible moment;

(c) A federal State Party to this Convention shall, at the request of any other Contracting State transmitted through the Secretary-General of the United Nations, supply a statement of the law and practice of the federation and its constituent units in regard to any particular provision of this Convention, showing the extent to which effect has been given to that provision by legislative or other action.

**Article XII**

1. This Convention shall come into force on the ninetieth day following the date of deposit of the third instrument of ratification or accession.
2. For each State ratifying or acceding to this Convention after the deposit of the third instrument of ratification or accession, this Convention shall enter into force on the ninetieth day after deposit by such State of its instrument of ratification or accession.

**Article XIII**

1. Any Contracting State may denounce this Convention by a written notification to the Secretary-General of the United Nations. Denunciation shall take effect one year after the date of receipt of the notification by the Secretary General.
2. Any Slate which has made a declaration or notification under article X may, at any time thereafter, by notification to the Secretary General of the United Nations, declare that this Convention shall cease to extend to the territory concerned one year after the date of the receipt of the notification by the Secretary General.
3. This Convention shall continue to be applicable to arbitral awards in respect of which recognition or enforcement proceedings have been instituted before the denunciation takes effect.

**Article XIV**

A Contracting State shall not be entitled to avail itself of the present Convention against other Contracting States except to the extent that it is itself bound to apply the Convention.

**Article XV**

The Secretary-General of the United Nations shall notify the States contemplated in article VIII of the following:

(a) Signatures and ratifications in accordance with article VIII;
(b) Accessions in accordance with article IX;
(c) Declarations and notifications under articles X and Xl;
(d) The date upon which this Convention enters into force in accordance with article XII;
(e) Denunciations and notifications in accordance with article XIII.

**Article XVI**

1. This Convention, of which the Chinese, English, French, Russian and Spanish texts shall be equally authentic, shall be deposited in the archives of the United Nations.
2. The Secretary-General of the United Nations shall transmit a certified copy of this Convention to the States contemplated in article VIII.